ዝክረ አውሊያእ

ዘመን ከዘመን እየከፋ እንጂ እየለማ አይመጣም ቢባል ለጆሮም ይገራል
ወርቁ ዘመን ሄዷል ከወርቅ ያልተናነሰውን ደግ ዘመን ተክቶ
ዛሬ በ2ተኛው ወርቃማ ዘመን ስለነበረ አንድ ዋርካ ላጫውታችሁ ወደድኩ
ይሉታል ፡የታቢኢዮች አባት
የንፁሃኖች ተምሳሌት
የውዱ ፍጥረት ጓዶች ተረካቢ
የብርሃናዊ እውቀት ካዝና
የኡለማኦች ማጠናከሪያ

ሸይኹል ኢስላም አቡ ሰኢድ አል ሀሰን ኢብን አቢ ሀሰን የሳር አል በስሪይ ረዲየሏሁ አንሁ ወቀደሰ ሲረሁ

ልሂቃን እንደተስማሙበት ከረሱል ሶሃቦች በኋላ ይህንን የታቢኢይ ሙክት የሚተካ ፍጥረት ዱንያ ላይ አልታየም
የእውቀቱ ምንጭ የሆኑት አራተኛው ኸሊፋና የሐቢብ ወንድምና ወዳጅ የሆኑት ዐሊዩል ሙርተዷ አል አከረም መሆናቸው የተሰውፍን ምሰሶዎች በማይንገዳገድ ችካል እንዲያቆም አስችለውታል
ከሱፊው ቅርጣን ለጉድ አሽትተዋል፡ከባህሩ ተግተዋል፡ ጥቁሩን ዘልማእ ቀደው አበጃጅተው ሰፍተዋል
የኛው ሐሰን

ከሊሎች ኢማሞች ለየት የሚያደርጋቸው ነገር እልፍ ነው፡ ኮርማው ኢላ ግን የሲልሲላው ጉዳይ ነው
በእርሳቸውና በሐቢባችን መሃከል ያለው ግርዶ ዐሊዩል አክረም ብቻ ናቸው፡ የተማሪያቸው ተማሪ መሆን ምን የከበረ እድል ነው!! በጠባህ ወተት ልክ የኢልሙ ትርትር ይግባልህም ተብለዋል ይባላል

የሱፊ ሊቃውንት እንደሚሉት የተሰዉፍ ጮራ የፊነጠቀችው ከዚሁ ኮርማ ነው፡ የጀነበሯ ድምቀትም በእርሳቸው ዙህድና ኢልም ስፋት ይለካል ፡የትኛውም ኦራኒይ ኢማም በሀሰን ጉያ ያደገ ጨቅላ ነው

ነሰባቸው ወደ ኢራቋ በስራ የሚጠጋ ሲሆን የተወለዱትም ከባርያ አባታቸው የሳር እንደሆነ ተከትቧል፡ እናታቸውም የእናታችን የምእመናን እናት ኡሙ ሰለማህ መውላ ስለነበረች ከረሱል ቤተሰቦች ጋር ጥብቅ ትሥሥር እንዲኖራቸው አስተዋፅኦ አድርጓል፡እራሳቸውም የሰይዲና ዘይድ ኢብን ሷቢት አል አንሷሪይ መውላ እንደነበሩ አይዘነጋም።

ሃፊዝ ኢማም አል ዘሃቢይ እንደፃፉት ከሆነ ጎልመስ መጠጥ ካሉ በኋላ ሸይኹል ኢስላም ኢማም አህሉል በስራህ ለመባል ብዙም አልፈጀባቸውም ነበር፡ ደግሞም ይገባቸዋል መች ለ30 ዐመታት ስቀው ያውቁና ፡ዐይናቸው ባፈሰሰውም እንባ ይሆናል የነጀይላን መርከብ የተሳፈረች!

በረሱል ጓዳ ተወልደው አዛው ግድም ያደጉት ታላቅ ኢማም ከአህለል በይት በረካ በመቋደስ የክብራቸው ማማ ለንፅፅርም አይነኬ ሁኖ ሰንብቷል፡ እንደውም ባንድ ወቅት በእናታችን ኡሙ ሰለማህ እቅፍ ተይዞ ወደ ክቡር ሶሃቦች ዘንድ ቀርቧል፡ዐሎታቸውንም ተቀብሏል ምን ይሄ ብቻ ከ ሰይድ ኡመር ኢብን አል ኸጣብ ፊት ቀርቦ በጨቅላነቱ ዱዐ ተደርጎለታል፡ ምን ይላል "አሏህ ሆይ በዲነል ኢስላም ፊቂህ በሰዎችም ዘንድ ተወዳጅ አድርገው".

የአሏህንም ቃል በሰይዲና ኡስማን ዘመን በ14 ዐመቱ ከልቡ አኖረ፡ የርሳቸውንም ኹጥባ ብዛት አጣጣመ፡ ከረመ አልፍ ከራረመ ፡ ከአጂላእ ሶሃቦች መሃል ሁኖ አደገ፡ የከራማን ሚዳ ጋለባት፡ አድሮ ሰነባበታት፡ ከዳመና ምንጣፍ ላይ የግንባሩን አሰር አኖረ ፡ እውቀትን ከሥራ ለጉድ አጣጣመ በኋላም የረሱልን ብርሃን ወራሽ ሁኖ አደረ ፡ በአንድ ወቅት ሰዎች ወደ ኸዲመ ረሱል ሰይዲና አነስ በድካማቸው ሃለት ላይ በመጡባበቸው ጊዜ የመለሱት መልስ እንደማጠናከሪያ ይወሰዳል፡'ወደ ሃሰን ሂዱ እኛ ስንረሳ እሱ ሓፍዟልና"
ሙሃመድ ኢብን ሰኢድ በጦበቃት እንዳሰፈረውም
ሐሰን አዋቂ፡ፈቂህ፡ጥበበኛ፡እንደበተ ርቱዕ፡ታማኝ እና መልከመልካም ሰው ነበሩ

ወደ እኛ በመጣ ጊዜ ዘመዶቹን ቀብሮ የመጣ
በተቀመጠ ጊዜም እንገቱን ሊቆረጥ ተጠባባቂ
እሳት በእርሱ ፊት በተነሳች ግዜም ለእርሱ እንጂ ለማንም ያልነደደች ያስመስልበት ነበር ፡ታዲያ ኢብን ኢማድ እንደሀሰን የሚሰራን አይተህ ታውቃለህን ብለው ይጠይቁታል ፡እርሱም ይመልሳል '' እንደርሱ የሚሰራ አይደለም የሚናገርም የትም አላገኝ '።ብሎ! !

ከበድሪይ ሶሃቦች ሰባ ያህሎቹን ሃድራ እንደተቃመሱ ከረሳቸው አንደበት ተነግሯል" ከ በድር ሶሃቦች 70 ዎቹን አግኝቻለው ሁሉም ሱፍ(ቆዳ) እንጂ ሌላን አይለብሱም ነበር"
የዚህች ሱፍ ነገር ስንቱ ይነገር፡ ስንቱ ፉደሏእ ይልበሰው ፡ደርቅ ደርቁን ከደረቱ ይነስንሰው??

የአሏህ ሰላም በባለውለታችን የበስራ ንጉስ ላይ ይሁንልን

. . . . . በአሏህ ፍቃድ የሚቀጥል ይሆናል ውዶች
መልካም ጁምዐ

. . . . .ካለፈው የቀጠለ ዝክረ አውሊያእ

ሐሰን አል በስሪይ ናቸው፡ ዙሪያቸው የደመቀው በእንስቶቹ ዋልታ ራቢዐ ፡ በነሀቢብ አል አእጀም ጥፍጥናን ከተፋቱት፡ ደግሞም ከጀነት ሙሽራዎች እኩሉ በድሪይ እኩሉ ኡሁዲይ 130 መውላዎች ፡ ፏፏቴው እስከ ሰይድ ጁነይድ አል ከቢር በሚደርሰው ፍሰት የታጠረ ሁነኛ የእርህማን ጁንድ!!

በሁፋዘቹ ኢማም አል ዘሃቢይ እና አል መናዊይ ከቀታዳህ በተነሳ ሽበር ቀጣዩ ተዘክሯል
በጊዜው ከነበሩ 7 የአራህማን ጓዶች ፡እነዚያ ሰዎች በነርሱ ሰበብ ዝናብ የሚዘንብላቸው የአሏህ እርዳታም የሚከፈትላቸው ፡በእርግጥም በሙተሰዊፎች ዘንድ በቅጡ ይታወቃሉ(ለሌላው ቢደበቁም) አብዳል ይባላሉ
ቀታዳህ አሁንም ይላሉ ፡ እነዚያ ሰባቶች አሏህ በእነርሱ ሰበብ በላእን የሚመልስላቸው፡ ህዝቡን የሚያጠቃቅምባቸው ናቸው፡ እርሱንም ከነዚያ ሰባቶች ውስጥ እገምተዋለሁ ፡ ሐሰን አል በስሪይ"

የቢሃር አል ዊላያህ ፀሃፊም ስለ አርባዎቹ አብዳሎች የሚያነሳውን ሐዲስ ዝርዝር ሰጥተውበታል
አብዳሎች 40 ሲሆኑ ኩባሮቹ 7 ናቸው
የነሐሰን ጭፍራ!

ተሰዉፍ ምንድነው ብሎ ባልተላወሰ አእምሮ ለሚጠይቅም እዚህ መንደር ቁባ መልስ ይዘግናል
ሱፊ የሚለውን ቃል ለመጀመሪያ ጊዜ የተነፈሱት ኢማም ሀሰን አል በስሪይ ናቸው የሚሉት ብዙዎች ናቸው፡ ተንፍሰውም አልተቀመጡም ኖረውታል ፡አብረውት ፈሰዋል እታች ከመሰረት በእንድዮሽ ተለስነዋል፡ ዘግነው ቀስመውታል

በአንድ ወቅት ሰዎች ወደርሳቸው ጠጋ በማለት ያ ሀሰን እኛ ከእንተ አንደበት የምንቀስማቸው እውቀቶች ከማንም ዘንድ ሰምተናቸው የማናውቃቸው እንግዳ ነገሮች ናቸው ሚስጥሩ ምንድነው ከማንስ ያዝከው??
ሀሰንም መለሱላቸው "ከሁዘይፈተል የማኒይ" የሰይደል ሙርሰሊን ሚስጥረኛ!

ቁውተል ቁሉብ በተሰኘው የኢማም አቡጧሊብ አል መኪይ ኪታብ ላይም ማረጋገጫ ሰፍሯል፥
ሀሰን አል በስሪይ ኢማማችን ነው፡ ይህንን የተሰዉፍ እውቀት በአሏህ ፍቃድ ከእርሱ ይዘናል በእርሱ ኩቱ እንቆማለን መንገዱንም እንከተላለን ከኢማም ወደ ኢማም ብንሸጋገር መድረሻችን እርሱ ይሆናል! ከታቢኢዮችም በኢህሳን የተመረጠው እርሱ ነበር ።

ስለምስክሮች ይህንን ካልን ስለርሳቸው ጥበባዊ ንግግሮችም እንድሁለት እንበል

ሃፊዝ አል መናዊይ በከዋኪቡል ዱሪያህ እንዳስቀመጡት ሐሰን አል በስሪይ እንዲህ ይላሉ፡
ሱፍ(ቆዳ) ሁሉንም ሰው አያስተካክልም፡ ውስጣዊ ንፅህና እና የነፍስ ክትትል(ሙራቀባ) ይጠይቃልና።

አንድ ሰው ወደርሳቸው በመምጣት ደረቅ ቆዳ የሚለብሰብትን ምክንያት ሲጠይቃቸው በምላሹ ዝምታን ይለግሱታል፡ ጠያቂውም በድጋሚ ጠንከር አድርጎ ሲይዛቸው ቀጣዩን ጣል አደረጉለት፡
إن قلت زهدا زكيت نفسي
أو فقرا أوضيقا شكوت ربي
ዙህድ ነው ካልኩህ ነፍሴን ማጥራት ነው
ድህነትና ምንድበና ካልኩህ ደግሞ ጌታዬን ስሞታ ማሰማት ይሆንብኛል።

ቢጨለፍ ኩር ማይለው የአስፊያኦቹ ሃድራ ብዙ ጉድ ይዟል፡ ማህተሙን አንግቦ ከራሱ የክብር ቱርባን ጠምጥሚል ፡ለእሻፈረኝ ባዮች መቆለፊያ ጨርቁን ተቀባብሏ

መውላና ዐሊዩል አክረም ከቁርዐን አናቅጽ አንድም መስመር አያውቁም ከአለቃቸው መውላና ሐቢብ አል ሙስጦፋ የተማሩት ቢሆን እንጂ ፡ይህንንም ብርሃን ያስተላለፉት አሁን እኛው ለምንዘክረው ሐሰን ነበር!
ሰለ ተቀባበሉት ጥምጣም ሊቃውንት ብዙ ብለዋል
ሰፋ አድርገው የተነተኑትም አሉ፡ ከሚስሮቹ አዋቂዎች ሃፊዝ አል ሱዩጢይ ይጠቀሳሉ
አራቱ አቅጣቦች ኢማም አብዱልቃዲር አል ጀይላኒይ፡ ኢማም አህመድ አል ረፋኢይ፡ ኢማም አህመድ አል በደዊይ እና ኢማም ኢብራሂም አልዱሱቂይ የጠመጠሙት የዐረብ ሻሽ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣው የሐሰን ቅሪት እንደሆነ ያትታሉ፡

. . . . . በአሏህ ፍቃድ በቀጣይ ፅሁፍ እናየዋለን!

መልካም ቀን ሰሉ ዐለይሂ

.....ካለፈው የቀጠለ ዝክረ አውሊያእ

ስለመኮንኖቹ ሰነድ የተዘከረውን እነሆ

ቢሃር አል ዊላያህ ላይ እነደሰፈረው ከሩአሳዎች ውስጥ ብዝሃ ሙሀቂቆች ከሰይድ ሀሰን ደጃፍ የሚደርስ ሲልሲላ እንንዳላቸው በአንድ ድምፅ ያስቀምጣሉ፡ ብዛት ያላቸው ጦሪቃዎችም(በተለይ ጦሪቀቱል በስሪይ) ተበለው የሚጠሩት በሰይድ ሀሰን ጓሮ በኩል አድርገው፡የአክረሙን በራፍ እንኳኩተው ወደ ዘይነል ዐለም የሚደርሱ እንደሆኑ ይነገራል፡

ይህንንም ትሥሥሮሽ በ3 አንኳር ፍሰቶች ከፋፍለው ያዩት ሊቃውንቶች አሉ፡ ቅርኝጫፉም የሚከተለውን ይመስላል

ሃድራው በሐቢቡላህ ተመሰረተ
ከዚያም ሑዘይፈተል የማኒይ ተከተል
ለጥቆ ሀሰን አል በስሪይ ተረከበ
ከዚያም ኢማም ሃሪስ አል ሙሃሲቢይ
ይህኛው ሲልሲላ በብዛት የተንሰራፋው በሰሜን አፍሪካ ሀገራት እንደሆነም ሰፍሯል

2ተኛው ቅርንጫፍ የሚከተለውን ይመስላል

በከውኑ ምሶሶ በፍጥረታት አለቃ ይጀምራል
ዐሊዩል ሀይደር ይከተላል አላህ ውጅሁን ይከርመውና
ሰይድ ሀሰን አል በስሪይ ይለጥቃሉ
ከዚያም ሀቢብ አል ዐጀሚይ
ከዚያም ዳዉድ አጣኢይ
ይህንንም ሰይድ መእሩፍ አል ከርኺይ ይረከቡና
ሰይድ ሲሪይ አል ሱቅጢይ ይቀበላሉ
በመጨረሻም ሲልሲላው በሰይዱና ጁነይድ አል ከቢር አል ባግዳዲይ ይጠቀለላል።

3ተኛው ቅርንጫፍ በውዱ ሀድራ ይበረካል
ቀጥሎ ሻዲመረሱል ደጉ አነስ ይቀበሉታል
ሲያልፍም ከሰይድ ሐሰን አቅፍ ይገባል ፡ሁሉንም መንፈሳዊ ቤተሰቦች አላህ ይውደዳቸውና።

አስተውላችሁት ከሆነ በእያንዳንዱ ሲልሲላ የአንድ ሰው ስም ሰፍሮ ይገኛል፡ ታዲያ የጦሪቃው ማጣፈጫ ቅመም ብንለው ምን ይመስላቹሃል!ሰይድ ሀሰን አል በስሪይ

ሙሪድ በሙሉ ልብ እንዲዘናፈል፡ ዐይኑን ያለመወላወል እንዲተክል ስለ ሲልሲላው ይህንን ያህል ካወራን ይብቃንና ወደ ከራማው መንደር እንግባ

ሙእጂዛ ለነቢይ እንደሆነች ሁሉ ከራማ ደግሞ የወሊይ እቃ ናት ይላሉ፡ሸሆቹ
በወፍ በረር ለመቃኘት ያህል እንጂ ይህንን ባት ለመጨረስ መቁጠር ትርፉ ድካም ነው

ኢማም ዘሃቢይ ከትበዋል
لما ظهر الحسن جآء كأنما كان في الأخرة
فهو يخبر عما عاين
ሀሰን ከሰዎች ዘንድ በታየ ጊዜ ከመጨረሻይቱ ዐለም የተመለሰ ይመስል ነበር ፡ስለርሷ የሚናገረውም ልክ እንተመለከተ ሰው ነበር ٤/٥٧٣ سير أعلام النبلاء

ሃፊዝ አል ዘሀቢይ ዳግም ከትበዋል
روي أنه أغمى عليه ثم أفاق إفاقة فقال
لقد نبهتموني من جنات وعيون ومقام كريم

በአንድ ወቅት ሰይድ ሀሰን እራሳቸውን እንደሳቱ ተወስቷል
በነቁ ግዜም እንዲህ ሲሉ ተናገሩ
በርግጥ ከተዋቡ ማሳዎችና ምንጮች አነቃችሁኝ፡ከተከበረም ሥፍራ ٤/٥٨٧ سير أعلام النبلاء

ኢማም አልነብሃኒይ የሚከተለውን ሰጅለዋል

لما بلغ الحسن قتل الحجاج لسعيد بن جبير
قال ،اللهم يا قاصم الجبابرة آقصم الحجاج
فما بقى إلا ثلاثا حتى وقع في جوفه الأكلة والدود فمات ،وهذه من كرامات حسن البصري

ሀሰን አል በስሪይ የሰኢድ ኢብን ጁበይር በሃጃጅ የመገደል ዜና በደረሳቸው ግዜ እንዲህ አሉ
ያ አሏህ አንተ የአምባገኖች ሰባባሪ፡ሀጃጅን ሰባብረው
ሀጃጅም በህይወት ከ3 ቀናት በላይ አልቆየም
ሆዱም የተላትል መከማቻ ሆነ፡ ሞተም ١/٣٨٩ جامع كرامات الأولياء

በድጋሚ ከኢማም አል ነብሃኒይ የተዘገበው ኸበርም እጂብ ያሰኛል

أنه كان ممن يصلي الصلوات الخمس بمكة -يعني وهو في البصرة - تطوى له الأرض ،فهو من أهل الخطوة

ሰይድ ሀሰን 5 ቱን ግዴታ ስግደቶች በመካ ይሰግዱ ነበር -የመኖሪያ ከተማቸው በስራ ሆና ሳለች-
ምድር ትጠቀለልላቸው ነበር፡ አህለል ኹጥዋ መሆናቸው እርግጥ ነውና المصدر السابق

ተፈከር ውድ አንባቢ
በኢራቅ እና በመከተል ሙከረማህ መሀካል ♦የ1963 ኪሎ ሜትር ርቀት አለ

ሱባሃን ላከበረው፡ የውዱን ሲፋ ለሱም ላበደረው

ለመደምደሚያ አንድ የከራም አላንጋ አላግቹ ፅሁፌን እቋጫለው፡

ኢማም አል መናዊይ ናቸው አሏህ ይውደዳቸውና
ورأى بعض الأولياء ليلة موته -أي إمام الحسن- أبواب السماء مفتحة وكأن منادي ينادى: ألا إن الحسن البصري قدم على الله وهو عنه راض

በዚግ ታላh ወሊይ ሞት ሊሊት ላይ የተወሰኑ ጓዶች ተመለከቱ
የሰማያት በር ተከፍተው
አንድ ተጣሪም ይጣራ ነበር
" አዋጅ አሏህ እርሱን የወደደው ሆኖ ሳለ ሐሰን ወደ ጌታው ቀድሟል!" ١٨٦-١/١٨٥ كواكب الدرية

ይቀረናል፡ ከሚዳው መጋለብ በረካ፡ትውስታቸው ጥጉብ፡ ትውፊታቸው ኩራት፡
የእጅ ጠበቡን ሳይዘክሩ ባለቤቱን አያሞካሹም ነውና ብዙ ይቀረናል
. . . . . በአሏህ ፍቃድ በቀጣይ ፅሁፍ የጀመርኩትን እጨርሳለሁ እስከዚያም አማን ሰንብቱልኝ።

صلو على الحبيب وعلى الأصفيآء

. . . . . ካለፈው የቀጠለ ዝክረ አውሊያእ

ደጉ ሀሰን ናቸው፡ እንቅዳ ከኡርፋናቸው፡
ሃያታቸውን ጠቅልለን ባናስሰውም የቻለነውን እንዘክራቸው
አካሄዳቸውን ያጠኑ ኡለማኦች መንሃጃቸው በአራት ፅኑ ምሶሶዎች የተጠናከረ ነው ይሉናል፡

የመጀመሪያው ማፅረፋ ነው፡ ጥልቅ እውቀት
ይህ ምሶሶ ከሁሉ ቀድሞ የተቸከለ፡ ከተግባር፡ ከፍርሃት፡ ከዙህድ ቀድሞ የተገነባ ነው፡ ኢማም ሀሰን አል በስሪይ በዘመናቸው ከነበረ የትኛውም አዋቂ እና ፈቂህ እጅጉን የሚበልጡ ለንፅፅር የማይቀርቡ ኮርማ ነበሩ
♦ ሃፊዝ አል ዘሃቢይ ከአውፍ አንስተው የዘገቡት እንደ ማመሳከሪያ ይያዛል፡
ما رأيت رجل أعلم بطريق الجنة من الحسن
ስለጀነት መንገድ ከሀሰን የበለጠ አዋቂ አይቹ አላውቅም
٤/٥٧٥ سير أعلام النبلاء

وكان سيد زمانه علما وعملا
ما رأيت أحد أشبه رأيا بعمر بن الخطاب منه -أي الحسن
በገፅታቸውና በበጎ አርአያነትም ከሰይዲና ኡመር ኢብን አል ኸጣብ ጋር ተመሳሳይ እንደነበሩ ተወስቷል
٤/٥٧٤ المصدر السابق

ኡለማኦችም ሐሰን አል በስሪይ ለመጀመሪያ ግዜ ስነ እእምሮ ጥናትን እና የነፍስ ማጥራትን እውቀት ተንትኖ እንደ እንድ ዘርፍ ያቀናጀው ሰው እንደሆነ ደርሰንበታል ይሉናል፡ የዘመኑ ኡብዳል እንደነበረም ተገልጿል ።

2ተኛው ምሶሶ ዙህድ ነው
ዙህድ ማለት የደረቀ ማኝክ፡ የቆሸሸ መልበስ ሳይሆን
አዋቂዎች እንደነገሩን
ኖረውትም እንዳሳዩን
ባለን ነገር መብቃቃትና በዱኒያ ላይ ተስፋን አለመጣል ነው
◆ ሐበታሙ ገንዘቡን በኪሱ ይዞ ፍፃሜውን ለአሏህ ከተወ ዚሂድ ነው
◆ድሃ የሚቀምሰው ባይኖረው እንኳ ሊተቀን ስለገንዘብ ካሰላሰለ የዱንያ ሰው ነው

ታዲያ የዙህድን ካባ ከደረቡ ሰማንያ እውቅ ታቢኢዮች መካከል ሰይድ ሀሰን አል በስሪይ አንጋፋው ኮሊ ናቸው ይላሉ ሃፊዝ አቡ ኑዐይም፡ከሶሃቢዩ ኡልቀመህ ኢብን መርሶድ ረዐ የተወሳውንም ይጨምራሉ፡ምንኛ ያምራል ከነቢ ሶሃባ ምስክርነት ማግኘት

فما رأينا من الناس كان أطول حزنا من حسن البصري
ከሀሰን አል በስሪይ የበለጠ ዳኢም ሐዘንተኛ አይተን አናውቅም። ٢/١٣٤ حلية الأوليآء

ሃፊዝ አል ዘሃቢይ ስለርሳቸው ዘግበው አይጠግቡም፡ ከመጦር ባስተላለፉት ኸበር ቀጣዩ ተዕፏል

دخلنا على الحسن نعوده فما كان في البيت شيء
لا فراش ولا بساط ولا وسادة ولا حصير إلا سرير مرمول هو عليه
٤/٥٧٢ سير الأعلام النبلاء

ሱብሃነሏህ ፡ለዚያራ እጓዳው የዘለቁ ጓዶች ጉድ ተመለከቱ
የተመቸ አንጣሪ ፍራሽ የለም
አንገት ማሞቂያ ትራስ አይታይም
የሚቆረቁር አፈር እንጂ የሚደላ ምንጣፍንም አላገኙም።

ስለዱንያ ሲያወሩም ከከባድ ማስጠንቀቂያ ጋር ነበር
من أكرمها يهن ولها في كل حين القتيل
ያከበራት ይዋረዳል፡ ለእርሷም በእያንዳንዷ ሴኮንድ ሚች አላት።

3ተኛው ምሶሶ ፍርሃት እና ሃዘንን ይጠቀልላል
እነዚህኞቹን ከታላላቆቹም ጥቂቶች እንጂ አያገኟትም
ፍርሃት ፍላጎትን ይንጣል ሀዘን ደግሞ የቀጣዩ ዐለም የደስታ ስንቅ ነው ፡ ሐሰን ትካዜያቸው መጨረሻ አልነበረውም፡ ስጋቸው ዱንያ ላይ ተቀመጠ እንጂ ሩሃቸው ሃሏ ብዙ ነው።

ኢማም ኢብን አል ጀውዚይ ከየዚድ ኢብን ሁውሸብ ባነሱት ኸበር፡
ما رأيت أخوف من الحسن وعمر بن عبد العزيز كأن النار لم تخلق إلا لهما
ከሐሰን እና ኡመር ኢብን አብዱልዐዚዝ የበለጠ የፍርሃት ባለቤት አላየሁም፡ እሳት ለእነርሱ እንጂ ለማንም ያልተፈጠረች እስኪመስልባቸው ድረስ ። صفة الصفوة لبن الجوزي

وروي عن يوسف بن أسباط أنه قال
(مكث الحسن ثلاثين سنة لم يضحك، وأربعين سنة لم يمزح).
ሐሰን አል በስሪይ 30 ዐመታትን ሳይስቅ ፡40 ዐመታትን ሳይቀልድ አሳልፏል ٣/٢٣٤ المصدر السابق

በሃዘናቸው ዙሪያ የመጡ አሰሮች ለመቁጠር ያዳግታሉ
በአንድ ወቅት እናቱን እንዳጣ ህጻን ተንሰቅስቀው እያለቀሱ ሳለ ሰዎች ምን አጋጥሞህ ነው ያ ሀሰን ይሏቸዋል እርሳቸውም በትካዜ መለሱላቸው፡
أخاف أن يطرحني غدا في النار فلا يبالي
ጌታዬ ነገን በእሳት ወርውሮኝ ሲያበቃ ግድም ባይሰጠው ብዬ እሰጋለሁ።
ፍርሃትና ሐዘን ለኛ መራር ቢመስሉም የቀልብ ጣፋጭ ምግቦች እንደሆኑም ተናግረዋል፡አሏህ ይውደዳቸውና።

4ተኛው ምሶሶ ተግባር ነው።
እስካሁን የተጠቀሱት ምሶሶዎች ያለዝህኛው ብቻቸውን መቆም አይቻላቸውም፡ ይበረከረካሉ
ስለ እምልኮ ትሩፋቶች እና ወደ አሏህ ስለመዘንበል በርካታ ወርቃማ ንግግሮች አሏቸው
من آنقطع إلى الله في مسجد للذكر والصلاة أقام الله له الدنيا خادمة

አሏህን ለማስታወስ እና ለስግደት ብሎ በመስጂድ ውስጥ ሁኖ ወደ አሏህ የተዘነበለ ሰው አሏህ ዱንያን የርሱ አገልጋይ ይደርጋታል። الكواكب الدرية ▫ للعلامة المناوي ١/١٨٢

وقال أيضا
المقيم في مسجد مرابط على طاعة الله يدفع الله به وبدعاءه البلاء عن العباد والبلاد
የአሏህ ትዕዛዛትን በማቋቋም እመስጂድ ውስጥ የሰነ ሰው፡ አሏህ በእርሱ እና በፀሎቶቹ ሰበብ የሌላውን ሰው እና ምድር ደህንነት ያስጠበቅለታል። الكواكب ▫ الدرية ١/١٨٢

ሊቃውንት ይሉናል
ይህ ታላቅ የከበረ አሰር እንጉበጋቢና ወሳኝ ነጥብን ይዟል፡ ተወሱል!!
አሏህ በሷሊሆች ሰበብ ሰውና ምድሩን ከቅጣት ከጠበቀ ባሮቹም በነዚህ ፈርጦች ወደጌታቸው መቃረብ ይወደድላቸዋል፡ሃሳቡ ቢሃር አል ዊላያህ አል ሙሀመዲያህ ገጽ 42 ላይ ሰፍሯል!!

የነዚህ ሷሊሆች የአምልኮ ቅመም ምን ነበር? ለዚህ ሁላ ጉዳጉድ ምን አነሳሳቸው?
የጀነት ፏፏቴ? የጀነም በለስ?
የኛው ሃሰን ገልፀውታል
لو علم العبدون أنهم لا يرون ربهم يوم القيامة لماتو
አባዶች በእለተ ትንሳኤ ጌታቸውን እንደማያዩ ቢያውቁ ወዲያው ይሞቱ ነበር። حلية ▫ الأولياء ٢/١٥٩

ይህንን አሰር ተንተርሰው ኡለማኦች ስለቀዳማውያን የሱፊ ኢማሞች የኢባዳ ሚስጥር መደምደምያ ሰጥተዋል
በጀሃነም አዘቅት ይወድቁና በዘይኑ ፊት ይነሳሉ
የጀባሩን ሲያስቡት ዳግም ዘፍ ብለው ወጅሁን ዙረው ይፈካሉ

ደግሞም ሀሰን ይገጥማሉ
المحب سكران لا يفيق إلا بمشاهدة محبوبه
ወዳጅ ሰካራም ነው ፡የሚወደውን ሲያገኝ እንጂ አይነቃም

ይህ ሰው ነው ያ 5ተኛው የሀቢብ የልጅ ልጅ መውላ ሙሀመድ አል ባቂር ፊት ስሙ የተወሳ ግዜ እንዲህ የተባለለት
ذاك الذي كلامه كلام الأنبياء
ይህ ሐሰን ነው ንግግሩ የአንቢያኦች ንግግር የሆነው
ነ

.....ካለፈው የቀጠለ ዝክረ አውሊያእ

ሐሰኔዋ አልቻልኖትምሳ
ድፍን ሸበር ማን ሊያነሳ?
የእርሶ እንዲህ ከሆነ
እንዴት ይሁን የዛ አንበሳ?

የጥበብ ምንጭ ከልሳናቸው ይፈልቅ ነበር ይባላል
የፍርሃት ጡሩሬ ከኩራት ቸነፈር አድኗቸዋል
የፍራቻ ታጅ ክበር ሁኗቸዋል
!!የሃዘን እምቢልታው ይነፋ የትውስታ ከበሮው ይደለቅ አንድ አዋቂ ሲለይ የሕዝብ ሞት ነውና

በአንድ ወቅት በበስሬ ውስጥ የዝናብ ጠብታ ይጠፋል፡ መሬት ጭንጫ ድንጋይ ሆነችባቸው፡ የረሃብ ግርፋቱን መቋቋም ያቃታቸው የበስሬ ነዋሪዎች ተሰባስበው ወደ አንድ አውላላ ጎረፉ ፡ ከፍ ያለ ሚንበርን ካበጁ በኋላ ወደ ሰይድ ሀሰን ተጠግተው ፡ ያ ሐሰን እባክህን ከጌታችን አስታርቀን ፀሎት እንድታደርስልን ዘንድ እንጠይቅሃለን
ሰይድ ሀሰን መለሱላቸው
آنفو الحسن من المدينة حتى يسقيكم الله، فإن آنقطاع الأمواع إنما هو سببه
ሀሰንን ከከተማችሁ አባሩት ያኔ አሏህ ውሃን ያጠጣችኋል
የዚህ ሁሉ ድርቅ ምክንያት እርሱ ነውና። تذكرة الأوليآء

ተፈከር፡ ከነዚህ ውብ ስብዕናዎች አንፃር እኛ የት ነው ያለነው
ስንቶቻችን ነን ነፍሳችንን አጥሪርተን ስናበቃ በወንድማችን ነውር ተተበትበን እራሳችንን ዝቅ ማድረግ ቋጥኝ መገፍተር የሆነብን
መውላና ዐሊይ አል አክረም وجهه كرم الله ያሉትን አትዘንጋ አሏህ ይውደድህና

طوبى لمن آنشغله عيبه عن عيب الناس

ውቧ የጀነት ዛፍ(ጡባ) በራሱ ነውሮች ተወጥሮ የሌሎችን ለማያነፈንፈው ትግባ!

ከጥንቱም የተባልነው፡ አንተ ሰባ ያህል የወንድሞችህን ነውሮች መቁጠር ከቻልክ ነውሮቹ በጠቅላላ የርሱ ሳይሆን ያንተ የግልህ እንደሆኑ ነው።

ወደ ሐሰን እንመለስ

በአንዳንድ አጋጣሚዎች ላይ የፍርሃታቸው ብዛት መጨረሻ ከጀሀነም አዘቅት የሚወጣውን ሰው ስም ልንገራችሁ ብለው ጓዶችን ከሰበሰቡ በኋላ የራሳቸውን ስም ይጠሩ እንደነበር ተከትቧል!

ተከታዩም ኸበር አጂብ ያሰኛል፡ ሰይድ ሀሰን ከሚህራባቸው ጥግ ተሰይመው አምልኳቸውን እያካሄዱ፡ ፀሎት እያደረሱ እና ስግደት እየፈፀሙ ነበር

ሳይታወቃቸው እጅጉን ከዱንያ ኪላ ርቀው ይንሰቀሰቁ ኖሯል፡ የሚያነቡት እንባ የጓዳቸውን ወለል ተርሶ በውጪ በኩል እንደ ዝናብ ውሃ ይንጠባጠብ ነበር፡

በሀሰን ደጃፍ የሚያልፍ አንድ ሰው ይህ ጡበታ ከልብሱ ላይ ሲያርፍ ይሰማውና፡ ጡበታው ከየት እንደመነጨ ዘወር ብሎ አይቶ ወደ ሰይድ ሃሰን ቤት ያመራል

ኳ ኳ ኳ ቤቶች እባካችሁን ክፈቱኝ

ማን ይሆን በዚህ ሰዐት እያሉ ሰይድ ሀሰን ይከፍታሉ

ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ፡ ከውጪ በኩል አንዳች ጡበታ እንዳረፈበትና ውሃው ንፀህ ይሁን ነጃሳ ይጠይቃቸዋል ፡ ሀሰንም ይመልሱለታል ምን መሰለህ ጃል፡

آغسله فإنه دمع عين العاصي لا تجوز الصلاة به

ጡበታ የነካብህን ልብስ እጠበው፡ ጡበታው የወንጀለኛ እንባ ነውና ፡ በዚህ ልብስ ስግደትን መፈጸም አትችልም

تذكرة الأوليآء ص٥٧

በአንድ ገጠመኝም ሰይድ ሀሰን አንድን ጀናዛ ለመሸኘት ከጓዶቻቸው ጋር አብረው ከሄዱ በኋላ ከሚች አጠገብ ተቀምጠው አፈር ውስጥ ተንሰቅስቀው አለቀሱ፡ አፈሩ ጭቃ እስኪሆን ድረስ፡ ከዚያም እንዲህ ሲሉ መከሩ፡

ወደዚህ ቀብር አትመለከቱምን፡ ይህ የዱንያ የመጨረሻ ኪላ ነው የአኺራ ደግሞ የመጀመሪያ

አደራ መጨረሻው ይህ በሆነ ዐለም እንዳትታለሉ

እንዴትስ መጀመሪያው ይህ የሆነው የቀጣይ ዐለምም አትፈሩም? የሁለቱንም ሀገሮች ሁኔታችሁን አስተካክሉ!

ይሄኔ ተሰብስቦ የነበረው ቀባሪ ለቅሶውን በአዲስ እሪ ይለው ጀመር! تذكرة الأوليآء ص٥٧

ሰይድ ማሊክ ኢብን ዲናር ሀሰንን አዋቂ እንዴት ነው የሚቀጣው ብዬ ጠየቅሁት ይላሉ

ቀልቡ ትግደልበታለች

የቀልብ ሞት ምንድነው?

የዱንያ ፍቅርና ክጃሎት

አብዱላህ ይዘግቡ፡

አንድ ቀን ወደ ሀሰን መስጂድ የሕብረት ሶላት ለመፈፀም በሌሊቱ ወቅት ወደዚያው አቀናው፡እንደደርስኩ ማንንም አላገኘውም፡የመስጂዱም በር ተዘግቶ ነበር

አንዳች ድምፅን ስለሰማው ወደ በሩ ተጠግቼ ውስጥ የሚሆነውን ለማድመጥ ሞከርኩኝ፡

የሀሰን ድምጽ ነበር፡ እርሳቸው ዱዐ ያደርጋሉ አሚንን የሚሉ ጀመዐዎችም ይከተሏቸዋል

ሁኔታው ግራ የገባቸው አብዱላህ ባሉበት ቁጢጥ ብለው የበሩን መከፈት መጠባበቅ ያዝሁኝ ይላሉ

ጥቂት እንደቆየው በሩ ተከፈተና ወደ ውስጥ ዘለቅሁ፡መስጂድ ውስጥ የነበሩት ግን ሰይድ ሀሰን ብቻ ነበሩ፡በእግራሞት ስለሆነው ሁሉ በነገርኳቸው ግዜም ረጋ ብለው መለሱልኝ፡

በእንያንዳንዷ ሌሊት አማኝ የሆኑ ጂኒዎች እኔ ዘንድ ይመጣሉ፡ ፀሎት እንዳደርግላቸውም ይማጸኑኛል እኔም አደርጋለው እነርሱም ከኋላዬ ይዐምናሉ አደራህን ይህንን ነገር ሚስጥር አድርገህ ያዘው። ٢٢١ المطبوع المرتجم

(እዚህ ጋር ምን ትዝ አለኝ መሰላችሁ፡ የጀመዐ ዱዐ

ሰይድ ሃሰን የጋኔን ጭፍራ ሰብስበው በተከበረ የአሏህ ቤት ውስጥ ቢድዐ..... መዐዘሏህ)

በሌላ አጃኢብኛ ኸበር ከሰይድ ሀሰን ጋር የጉዞ ሻንጣ ሸክፈው ለሀጅ መንገድ የወጡ ጀመዐዎች ጭው ያለ በረሃን አጋምሰው ወደ አንድ የውሃ ጉድጓድ ይደርሳሉ፡በደስታ ጉድጓዱን ቢቃኙ እውስጥ ያገኙት የበረሃ ጠጠር ብቻ ነበር

ይሄኔ ሐሰኔዋ አብሽሩ አሏቸው

በሶላታቸው ወሰሏቸው

እኔ ስሰግድ እናንት የቻላችሁትን ውሃ ቅዱ (ሱብሃን የቂን)
እንዳሏቸው የእርሳቸውን ተክቢራ ጠብቀው የሚፈልቀውን የጉድጓድ ውሃ ተያያዙት፡ እስኪበቃቸው ተጋቱት፡ተጣጡ፡ በቡሃቃዎቻቸው ሞላልተው፡ ውሃው ጫፍ ደርሶ ተራጨት።

تذكرة الأولياء. ص ٥٩

ዳግም አይን ከሚበለጥጥ ኸበር ላይ ደርሰናል

ባለታሪኩ አቡኡመር ናቸው፡ በጊዜያቸው እውቅ የቁርዐን አስተማሪ ነበሩ የገጠማቸውን እንደሚከተለው ይተርካሉ፡
በማስተምርበት መድረሳ ውስጥ አንድ መልከመልካም ወጣት ነበር፡ ፊቱ እጅጉን የተዋበ
እኔጋር እየተመላለሰ መቅራት ከጀመረ ሰንበትበት ብሏል
በአንድ ወቅት ወደ እኔ ተጠግቶ በመማር ላይ እያለ ሽይጧን ፊቱን አሰማምሮ ትብታቦውን አቀረበልኝ፡ በሳምኩት ብዬም አሰብኩኝ ፡በዚችው ቅፅበት አሏህ ጥሬ የሀፊዝኩትን ቁርዐን ከልቤ ላይ ጠራርጎ ሲወስደው ታወቀኝ፡በጣም ተደናገጥኩኝ ልቤም በፍርሃት እሳት ትቃጠል ያዘች፡

ቀናቶችን ካብሰለሰልኩ በኋላ ወደ ሀሰን ዘንድ ሂጄ የገጠመኝን በሙሉ እንባዬን እያፈሰስኩ በቁጭት ነገርኩት ዱዐ እንዲያደርግልኝም ጠየቅሁት ፡ ሀሰንም ባዘነ ድምጽ መለሰልኝ ፡" አዝናለው፡ ጥያቄህን ለማግኘት የግድ የአሏህን ቤት መዘየር ይኖርብሃል፡ ወቅቱም ስለሆነ ግዜ ሳታጠፋ እንዲን ጭፍራ ተቀላቅለህ ጉዞህን ጀምር፡እዚያ እንደደረስክ በመስጂደል ኺይፍ አንድን ሽማግሌ ታገኛለህ፡ ከሚህራቡ ባጥ ስር የሚቀመጥ ሰው ነው፡ አደራህን እን

ዳትረብሸው፡ አምልኮውን ሲጨርስ ተጠጋውና የደረሰብህን ሁሉ እጫውተው እርሱ ዘንድ መፍትሄ አይጠፋም፡
አቡ ኡመር ይቀጥላሉ
ይህንን ስሰማ በተስፋ ፊረስ ወደ መካ ጋለብኩኝ፡ እንደደረስኩም የአሏህን ቤት ዘየርኩ፡ ሥነስርዐቱን አሟልቼ ከጨረስሁ በኋላ ሀሰን የጠቆመኝን መስጂደል ኺይፍ አፈላልጌ አገኘሁት፡ዘለቅሁበትም
ገና ከመግባቴ የተባልኩት ሽማግሌ ከእንድ ምሶሶ ተንተርሶ ተቀምጧል፡ ዙርያውን ተማሪዎቹ የሚመስሉ ሙሪዶች ከበውታል ፡ይህ በእንዲህ እንዳለ አንድ ባለግርማ ሰው ወደ መስጂዱ ሲያኮበኩብ ሽይኹ እና በዙሪያው ያሉት ተማሪዎች ሁሉ ብድግ አሉ፡ ከፊትለፊታቸውም ሁኖ የዙህርን ሶላት መርቶ አሰገዳቸው ፡እንደጨረሰም ብዙ ሳይቆይ ተሰናብቷቸው ሄደ፡ የቀድሞውም ሽይኽ ብቻቸውን ተቀመጡ፡
ይህንን እድል ተጠቅሜ ወዳሉበት ግድም ሂጄ ተዋወቅኳቸው የገጠመኝን ሁሉ በብሶት ለዛ አጫወትኳቸው፡ እጃቸውን ወደ ሰማይ ከፍ አድርገው ይማፀኑ ጀመር፡ወሏሂ ገና እጃቸውን ከማንሳታቸው ልቤ ስትሸረህ ተሰማኝ፡ ጠፍቶብኝ የነበረው የአሏህ ቃል ከልቤ ጓዳ ሲዘልቅ ደስታዬን መቆጣጠር አቃተኝ፡ የመስጂዱ አፈር ላይ ወድቄ ተንፈራፈርኩ ደግሞም የሽይኹን እግር ሳምሁ፡
ፀሎታቸውን እንደጨረሱ ወደርሳቸው ማን እንደላከኝ አጥብቀው ጠየቁኝ፡ በመጨረሻም ሀሰን አል በስሪይ እንደሆነ ነገርኳቸው ፡ፊታቸው ፈገግ እንዳለ ቀጣዩን ተነፈሱ፡ ወይኔ ሀሰን ኢጋለጠኝ
إن الرجل الذي جآء إلينا وأكرمناه وصلينا معه الصلاة كان هو الحسن يجيء إلينا كل يوم ويصلي بنا الظهر ثم يصلي العصر باالبصرة
من كان له إمام مثل الحسن كيف يحتاج إلى غيره ولا يستدي منه؟!

ልጄ ሆይ ቅድም ወደኛ ዘንድ ሲመጣ በክብር የተቀበልነው የዙህር ሶላትንም ያሰጋገደን ሰው እርሱ ያንተው ሀሰን አል በስሪይ ነው (በበስራና መካ መሃከል የቀናት ጉዞ እንዳለ ማጤን ግድ ይሏል)
የዐስር ሶላትን የሚሰግደው በበስራ ከተማ ነው
ሀሰንን የመሰለ ኢማም ያለው ሰው እንዴትስ ከርሱ ውጪ ሌላን ይፈልጋል፡ ዱዐንስ ከሌላ ይፈልጋል?
تذكرة الأولياء
የወሊዮቹ ብድር በምድር እንዲህ ነው
ጉድ ከዚህ ቁሷ ስንቱን እንማር
ርቀት ቦታ እና ድካም አይደለም ለኸሊቁ አንዳንዴም ለደካማው ፍጡር እጅ ይሰጣሉ፡በአሏህ ፍቃድ
አቤት መተናነሳቸው ‼ ጠቀማቸው ካህለሱፋ መቀማመጣቸው

ቀጥል፡ ጂራፉን አፍታታ
ዳግም ተዝኪራው ላይ እንደትሰጀለው ሀሰን አል በስሪይ ጓዶቻቸውን ሰብስበው የለገሷቸው የሰላ ምክር ነበር
ንገሩኝ ከረሱል ሶሃቦች ምናችሁ ነው የሚመሳሰለው?
!! እናንት እነርሱን ብታዩ ኑሮ የለየላቸው መጅኑኖች ትሏቸው ነበር
!!እነርሱ እናንተን ቢያዩ ደግሞ እናንተ ሙስሊሞች አይደላችሁም ይሏቹ ነበር
واشتغلو بالدين واليقين
وأما نحن فمشغولون بجيفة الدنيا وحطامها كبعض الطيور الواقع على الجيف
እነርሱ ስለእስልምና እና እርግጠኝነት ለፉ ደከሙ
እኛ ደግሞ በዱንያ ጥምብ እና ስብርባሪ ተጠምደን ሰዐት አጣን፡ ልክ ጥምብ እንደሚያነሳው አሞራ!

ስለወረኛ የወሬ ቋቶች ሲያስጠነቅቁም ቀጣዩን ብለዋል
من جآء إليك بكلام الناس يمشي بكلامك إلى الناس
የሰዎችን ወሬ ይዞ የመጣልክ ያንተንም ወሬ ይዞ መመለሱ አይቀሬ ነው

በአንድ ወቅት በመቃብሮች መሃከል ቁጭ ብሎ የሚመመጉብን ሰው ተመልክተው የተናገሩት አይረሳም
هذا منافق تطيق نفسه تلذذ بالطعام وعنده أهل الماقابر
وكيف
لو كان يؤمن بلأخرة والعذاب ما أكل هناك
ይህ ሰው ሙናፊቅ ነው፡ እንዴትስ በመቃብር ባልተቤቶች ፊት ቁጭ ብሎ ምግብን ማጣጣም አስቻለው
በቀጣዩ ዐለምና በቀብር ቅጣት ቢያምን ይህንን ባላደረገ ነበር።

እንግዲህ የወጉን ከአብዳሎች ማሳ ኮርኩረናል፡ ብቸኝነት እንድረመጥ የገረፋቸው ሐሰን አልበስሪይ ይህንሁላ
ጉዳጉድ ከተሰማላቸው ከሰዎች የሚቀላቀሉ እና ኑሯቸውን ለመሰለል ቀላል የሆኑ ሰው ቢሆኑ ኖሮስ ምን ይሰማ ነበር
በመጨረሻም የማይቀረውን ሞት መጋፈጣቸው አልቀረም፡ ኸበሩን እነሆ

በሞታቸው ሓድራ ላይ በበስራ ነዋሪዎች ተከበው ባሉበት አንዲትን ቃል ፈገግ ብለው በሰመመን ተናገሩ"
የትኛዋ ወንጀሌ"
በህይወታቸው ለ30 ዐመታት ሳይስቁ በሞት አፋፍ ላይ ሁነው በፈገግታ ያቺን ቃል ተንፍሰው መሞታቸው
ያስገረማቸው ሷሊሆች በሞቱበት ሌሊት በህልማቸው እዩኣቸው፡የነገሩን ሚስጥርም ጠየቋቸው፡ ሀሰንም ይህንን መለሱ

سمعت صوتا يقول يا ملك الموت شدد عليه
فقد بقي عليه ذنب فتبسمت فرحا من أن بقي علي ذنب واحد ثم قلت أي ذنب وخرجت من الدنيا

አንድን ድምጽ ሰማው" አንተ የሞት መልዐክ ሆይ ስቃዩን አበርታበት አንዲት ወንጀል ቀርታበታለችና"
ይህንን ስሰማ በሀሴት ተሞላው፡ አንድ ወንጀል ብቻ ስለቀረኝ
የትኛዋ ወንጀሌ እንደሆነች በአግራሞት ጥያቄ "የትኛዋ ወንጀሌ ትሁን"እያልኩ የዱንያን ኬላ ተሰናበትኩኝ። تذكرة الأولياء
ገ፱ .ص (በሌላ የረሱል ሐዲስ የሙአሚን የጋርጋራ ስቃይ ወንጀሉን የሚያሰርይለት ሊሆን እንደሚችል ተገልጿል
ኢህያእ ኡሉሙዲን)

ከሰማያት አጥናፍም ተሰማ "አዋጅ ሀሰን በጌታው የተወደደ ሁኖ ወደርሱ ቀድሟል"

በ21ኛው ዐረ ተወልደው በ110ኛው ላይ በኸሚስ ማለዳ
ከ63 የሚዘሉ ሽይኾቻቸውን ጥለው፡ እልፍ አላፍ ተማሪዎቻቸውን አስለቅሰው፡ በስራን አስከ መዲና ጫፍ አስከፍተው
89የዱንያ ዐመታትን ፈይዳቸውን ዘርተው የወረሱትን ኑር ለቀጣይ አንበስ አስረክበው፡ ወዳጃቸውን ሀቢብ ተቀላቅለዋል፡
ዳግም ወደማያዝኑበት ዐለም።
أَلَآ إِنَّ أَوْلِيَآءَ ٱللَّهِ لَا خَوْفٌ عَلَيْهِمْ وَلَا هُمْ يَحْزَنُونَ
ንቁ! የአላህ ወዳጆች በእነሱ ላይ ፍርሃት የለባቸውም፤ እነሱም አያዝኑም። ዩኑስ÷ 62
በሌላ ወሊይ ታሪክ ዕሁፉ ሊቀጥል ይችላል፡ በአሏህ ፍቃድ

በዚህ ዕሁፍ ውስጥ ማስተካከያ እርማትና ሌላም ሃሳብ ያላችሁ ከአውፍታ ጋር @AYOUMY ላይ መልዕክታችሁን
አድርሱኝ።
ለዕሁፉ የተጠቀምኳቸው ዋቢዎች በዋነኝነት المحمدي بحار الولاية እና የጥንቱ ፈረዱዱን አጣር
تذكرة الأولياء የተሰኙ ኪታቦች ናቸው።

ኡለማኦቻችንን የምናከብርበት የወገብ እሳት አጥፊ ስንክሳር መሆኑን ወዲያ ጥለን የሙግሳ መለከት
የምናስጮህላቸው ታሪካቸውን ከእራሳችን አልፈን ለከሃዲያን እጅ መንሺያ የምናሳርፍላቸው ሸጋ ሙሪዶች ያረገን ዘንድ
አሏህዬን እየጠቅሁ ጽሁፌን እቋጫለሁ፡
!!አሏህ ብቸኛው አዋቂና ጥበበኛው ነው
صلو على الحبيب وعلى الأصفيآء